ከሙስና የጸዱች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 34 ጥር 30/2018 ዓ.ም

## በውስጥ ገፆች

በተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በብቃት ለመፈጸም የአመራሩ ድርሻ ወሳኝ ነው
ገጽ 2

የዲጂታል ቴክኖሎጂ ትግበራ የሙስና ተጋላጭነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ይገኛል
ገጽ3

ኮሚሽኑ በመጀመሪያ ስድስት ወራት ያከናወናቸው ውጤታማ ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተገለጸ!
ገጽ 5

በታማኝነታቸው በአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ እውቅና ያገኙት-አቶ አማረታደሰ
ገጽ 6

## ጠንካራ ተቋማት ማለት ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂ እና ሥነ-ምግባር ተደምረው ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉባቸው ማዕከላት ማለት ናቸው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) "በመደመር መንግሥት" መጽሐፍ እና መደመር ፍልስፍና ውስጥ የተቋማት ግንባታ የሀገር ግንባታ ዋና ምሰሶ ተደርጎ ተወስዷል:: መንግሥትም ይህንን እሳቤ በተግባር በመተርጎም፣ ተቋማትን ገለልተኛ፣ ዘመናዊ እና ውጤታማ የማድረግ ሪፎርም ሥራዎችን አከናውኗል::



እነዚህ ሥራዎች በግለሰቦች ፍላጎት ላይ ሳይሆን ግልጽ በሆኑ ሕጎችና መመሪያዎች ላይ እንዲመሠረቱ በማድረጋቸው፣ አስተማማኝ ተቋማዊ መረጋጋት ተፈጥሯል:: ጠንካራ ተቋማት ማለት ዕውቀት፣ ቴክኖሎጂ እና ሥነ-ምግባር ተደምረው ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉባቸው ማዕከላት ማለት ናቸው:: በመደመር መንግሥት እሳቤ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማትን በቴክኖሎጂ የማዘመንና ለሀገራችን ብልጽግና ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ የልህቀት ማዕከላትን የመገንባት ሥራዎች፣ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ያላትን ተወዳዳሪነት አሳድገዋል::

እነዚህ የተቋማት ግንባታ ሥራዎች መጨረሻ ግባቸው የሕግ የበላይነት የነገሠባትና ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት የበለፀገች ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ ነው::

## 4ኛው ዙር አገርዓቀፍ የሙስና ግንዛቤ ዳሰሳ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ላይ ውይይት ተካሄደ

4ኛው ዙር አገርዓቀፍ የሙስና ግንዛቤ ዳሰሳ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ላይ ከጥናት ምሁራንና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል:: ውይይቱ የዜጎችን የሙስና ወንጀል የግንዛቤ ደረጃ ለመለካት የሚከናወነውን 4ኛው ዙር አገርዓቀፍ የዳሰሳ ጥናት የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በተገኘው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ላይ ከጥናት ምሁራንና ባለሙያዎች ጋር ለመገምገም ተችሏል::

በውይይቱ ላይ የተገኙት የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) እንደገለጹት፤ ይህ ጥናት በአገሪቱ ያለውን የሙስና ግንዛቤና ተጋላጭነት በትክክል የሚያመለክት ነው:: ጥናቱ በሳይንሳዊ መንገድ የተሰበሰበና መረጃን መሠረት ያደረገ በመሆኑ፣ በቀጣይ የፀረ-ሙስና ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ ትልቅ ግብዓት ይሆናል ብለዋል:: ኮሚሽነሩ አክለውም ጥናቱ ዜጎች ስለ ሙስና ያላቸውን አመለካከት፣ የወንጀሉን ስርጭትና መከላከያ መንገዶችን በጥልቀት በመተንተን አገራዊ የግንዛቤ ደረጃቸውን በግልጽ እንደሚያሳይ ተናግረዋል:: ይህ 4ኛው ዙር አገርዓቀፍ የዳሰሳ ጥናት ውጤት በቅርቡ ተጠናቆ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ገልፀዋል::






**ትውልድን በሥነምግባር፤ ተቋምን በአሰራር!**

**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

# በተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በብቃት ለመፈጸም የአመራሩ ድርሻ ወሳኝ ነው - ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-መስና ኮሚሽን ለፌደራል ዘርፎች/ተቋማት የሥነምግባር ግንባታና ፀረ-ሙስና ሥራ አሥፈጻሚዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሰጥቷል::

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በብቃት ለመፈጸም የአመራሩ ድርሻ ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፥ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል::

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም መድረኩ ለሥራ ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን የምናገኝበትና ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ቀጣይ በምንሰራቸው ተግባራት ላይ ትኩረት ለማድረግ ያስችላል ብለዋል::በኮሚሽኑ የሙስና መከላከልና ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽንር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው













በበኩላቸው የሙስና መከላከል ስራ ውጤታማ እንዲሆን አመራሩን የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል::

በመድረኩ በየዘርፎች በመጀመሪያው ግማሽ በጀት ዓመት የተሰሩ ውጤት አመላካች ተግባራት ቀርበው የተገመገሙ ሲሆን በአፈጻጸሙ የነበሩ ጠንካራ ጎኖች ፣ የታዩ ድክመቶችና የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሳቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል:: መድረኩ ለቀጣይ ስራዎች ትምህርት የሚወስድበትና ሥራዎች ምን ላይ እንዳሉ የሚያሳይ እንደሆነ ተሳታፊዎች ገልጸዋል::



## ከሥነምግባር ጋር በተያያዘ በ4 ሺህ 244 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በ3 ሺህ 63 የተቋሙ ሠራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል - የገቢዎች ሚኒስቴር

የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ በቢሾፍቱ ከተማ አካሂደዋል::

በመድረኩ ባለፉት 6 ወራት ደረሰኝ ሳይቆርጡ ግብይት በፈፀሙ ግብር ከፋዮች ላይ ከ34 ሚሊዮን ብር በላይ ቅጣት መሰብሰቡ ተገልጿል::

በሌላ በኩል በሐሰተኛ ደረሰኝ ግብይት እንዲሁም በሕገወጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እና ያልተገባ ኪሳራ ሪፖርት ላይ በተደረገ ምርመራ መንግሥት ሊያጣው የነበረውን 14.4 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን ከቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል::

በበጀት ዓመቱ 6 ወራት ግብር ከፋዮች በኢሌክትሮኒክ ዘዴ ብቻ ከ166 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ ተፈፅሟል::

ከተመዘገቡ 40 ሺህ 703 ግብር ከፋዮች ውስጥ 33 ሺህ 345 ግብር ከፋዮች በዚህ ቴክኖሎጂ ተስተናግደዋል::

ከሥነምግባር ጋር በተያያዘ በ4 ሺህ 244 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በ3 ሺህ 063 የተቋሙ ሠራተኞች ላይ በጥቅሉ በ7 ሺህ 307 ግብር ከፋዮች እና ሠራተኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን የገቢዎች ሚኒስትር ገልጸዋል::





## ጉቦኝነትና ብልሹ አሰራርን በዘመናዊ አሰራር እና በሕዝብ ተሳትፎ ለማምከን መግባባት ላይ ደርሰናል

ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ጉቦኝነትና ብልሹ አሰራርን በዘመናዊ አሰራር እና በሕዝብ ተሳትፎ ለማምከን መግባባት ላይ መደረሱን የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል:: ከንቲባዋ በትጋት አዲስ አበባን ወደ ላቀ ስኬት!" በሚል መሪ ሃሳብ ባለፉት ቀናት ስናካሂድ የነበረውን የከተማችንን የ2018 በጀት ዓመት የ6 ወራት የመንግሥትና የፓርቲ ስራዎች አፈፃፀም ግምገማ በስኬት አጠናቅቀናል ብለዋል::

በግምገማውም ባለፉት ስድስት ወራት በሁሉም ዘርፍ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ውጤት መምጣቱን እንደተግባቡ ተናግረዋል:: ከሕዝቡ ቅሬታ ከሚቀርብበት የአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር በ'መሶብ' የአገልግሎት አሰጣጥ የ94 በመቶ የህዝብ እርካታ ማግኘት መጀመራችን ለቀጣይ ስራችን ትልቅ ስንቅ መሆኑን በማህበራዊ ሚዲያ የትስስር ገፃቸው አስፍረዋል:: በቀጣዮቹ 6 ወራትም ትኩረት የሚሹ የአመራር አፈፃፀም ልዩነቶችን በማጥበብ፣ ተቋማዊ ግንባታን ለማጠናከር፣ ጉበኝነትና ብልሹ አሰራርን በዘመናዊ አሰራር እና በሕዝብ ተሳትፎ ለማምከን መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል::

የከተማችንን ነዋሪዎች በተሻለ ትጋትና ታማኝነት ለማገልገል፣ የመረጃ አያያዝን ለማዘመን እንዲሁም የኑሮ ውድነትን ጫና በመቀነስ የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክረን ለመስራት መግባባት ላይ የተደረሰበት ውጤታማ መድረክ እንደነበርም ጠቁመዋል::

## ዲጂታላይዜሽን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በማስቀረት

በኦሮሚያ ክልል ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ስትራቴጂ ጋር በተጣጣመ መልኩ የዲጂታላይዜሽን ስራዎች በትኩረት እየተሰሩ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ገልጿል።

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር መኮንን በየነ ለፋና ዲጂታል እንደገለጹት፥ በክልሉ በሁሉም ዘርፍ ዲጂታላይዜሽንን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች እየተከናወኑ ነው። በተለይም የመሬት አስተዳደር ዘርፉ ሙሉ ለሙሉ ከእጅ ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ በዲጂታል ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል። በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የፋይዳ ዲጂታል መታወቂያን ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ብለዋል።

የዲጂታል መሰረተ ልማትን ለማስፋፋት የክልሉ መንግስት በስፋት እየሰራ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፥ ዲጂታላይዜሽን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በማስቀረት ለኢኮኖሚው ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ጠቁመዋል::ይህንን ከፍተኛ ሚና ለሕብረተሰቡ በማስገንዘብ ረገድ ተከታታይ ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን አስታውሰው፥ በዚህም ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን ተናግረዋል።ለአብነትም በከተሞች የሚኖረውን አብዛኛውን ማህበረሰብ የፋይዳ መታወቂያ ባለቤት ማድረግ መቻሉንና የዲጂታል ክፍያ ስርዓት ተጠቃሚዎች ቁጥር እያደገ መምጣቱን አንስተዋል። የተቋማትን አገልግሎት ወደ ዲጂታል ስርዓት ማስገባት ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የጸዳ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ያስችላል ያሉ ሲሆን፥ ሕብረሰተቡ ይህንን በመገንዘብ ዲጂታል ስርዓቱን እንዲቀላቀል ጥሪ አቅርበዋል።







## የዲጂታል ቴክኖሎጂ ትግበራ የሙስና ተጋላጭነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና እየተጫወተ ይገኛል

ኮሚሽኑ በተቋማት የሚያካሂደው የሙስና ተጋላጭነት ጥናቶች የመከላከል ስራውን ውጤታማነት ማሳደጉንም ተጠቁሟል:: መንግስት በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስና፣ የመልካም አስተዳደርና መሰል ድርጊቶችን ለመከላከል የተለያዩ ዘመናዊ አሰራሮችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል:: በዚህ ረገድ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ትግበራ ሙስናን ከመከላከልና ግልጽነትን ከመፍጠር አንጻር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው:: ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረጋቸው ለብልሹ አሰራር የሚመች ሁኔታን ማጥበብ ይቻላል::

ይህ የዲጂታላይዜሽን ስራ ዜጎች ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረገም ይገኛል:: ይህ ተግባር በፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እየተካሄደ ካለው የሙስና ተጋላጭነት የልየታ ጥናት ጋር ተዳምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የፀረ-ሙስና ንቅናቄ ይበልጥ ውጤታማ እያደረገው ይገኛል:: በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ለኢዜአ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ ለሙስና ወንጀል ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን በማሻሻል ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል::

በተለይም በዜጎች ፍትሃዊ የአገልግሎት ተጠቃሚነት ላይ እንቅፋት የሆኑ ብልሹ አሰራሮችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ የልየታ ጥናቶች እየተካሄዱ መሆኑን ጠቁመዋል:: እስካሁን ባለው ሂደት በ14 ተቋማት ላይ ጥናት ተካሂዶ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል:: ጥናቶቹ ቁልፍ በሆኑ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የሙስና ተጋላጭነት መንስኤዎችን በግልጽ የሚያሳዩ መሆኑን ጠቅሰው ጥናቱን ተከትሎ ተቋማት አሰራራቸውን እንዲፈትሹ ከማድረግ ባለፈ ተጨባጭ ለውጦች መታየታቸውንም ገልጸዋል::

ይህን ተከትሎም የተቋማት የሕግ ማሻሻያ፣ የአደረጃጀት ለውጥና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዲዘረጉ ማስቻሉን ጠቅሰዋል:: የጥናት ውጤቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰው ኮሚሽኑ እርምጃዎቹ በአግባቡ መወሰዳቸውን በጥብቅ ይከታተላል ብለዋል:: በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የተደረገው መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተቋማት የተቀናጀና የተቀላጠፈ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ተገልጿል::

አሰራሩም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ዜጎች ያለእንግልት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ላይ መሆኑንም ተናግረዋል:: ኮሚሽኑ እያከናወናቸው ያሉ የጥናትና የማሻሻያ ስራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙስናን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ እያገዙ እንደሚገኙም ጠቁመዋል::



## ሙስናን የሚቀንስ ከሰው ንክኪ ነጻ የሆነ የፖሊስ ጣቢያ አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው ተባለ

የፖሊስ ጣቢያው ከወንጀል ሪፖርት ባሻገር የተለያዩ ክፍያዎችን ጨምሮ እስከ 46 የሚደርሱ የመንግስት አገልግሎቶችን መስጠት የሚችል ሲሆን፣ ቴክኖሎጂው የሰው ንክኪን በመቀነስ ሙስናን ለመከላከል እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ተገለጽዋል::


በአፍሪካ የመጀመሪያ እንደሆነ የተነገረለትና ሰው አልባ ወይም ዘመናዊ የፖሊስ ጣቢያ (Smart Police Station) በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑን ከኢትዮ ኤፍ ኤም የታዲያስ አዲስ ዝግጅት ክፍል ጋር ቆይታ ያደረጉት በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ መምሪያ ኃላፊ ኮማንደር ደምስ ይልማ ተናግረዋል:: ኮማንደሩ እንደገለጹት፣ ይህ ዘመናዊ ጣቢያ ከዚህ ቀደም ከነበረው አሰራር በተለየ መልኩ ተገልጋዮች በአካል ፖሊስን ሳያገኙ፣ በዲጂታል መንገድ በዋናው ማዕከል ከሚገኙ የፖሊስ ኦፊሰሮች ጋር በቪዲዮ እና በድምጽ በመገናኘት ጉዳያቸውን የሚያስፈጽሙበት ነው::

ምንም እንኳን ወንጀልን ለመከላከል የሰው ኃይል አስፈላጊ ቢሆንም፤ ይህ ቴክኖሎጂ አንድ ግለሰብ ወንጀል ሲፈጸምበት በፍጥነት ሪፖርት በማድረግ እና በጂፒኤስ (GPS) እንዲሁም በካሜራ የታገዘ መረጃ ለፓትሮል ፖሊስ በማስተላለፍ ወንጀለኞችን በፍጥነት ለመያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውተገልጿል:: አገልግሎቱ ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ታስቦ በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ ሱማሊኛ፣ እንግሊዝኛ እና በሌሎችም ቋንቋዎች እንደሚሰጥ ገልጸዋል:: ጣቢያው ከኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ መተግበሪያ (EFP App) ጋር በመቀናጀት በስማርት ስልኮች ላይ ያለውን አገልግሎት እዛው በሚገኙ ማሽኖች ማግኘት እንደሚቻልም አንስተዋል::

በቦሌ ድልድይ አካባቢ የሙከራ ፕሮጀክት ሆኖ የተጀመረው ይህ አገልግሎት÷ ውጤታማነቱ ታይቶ እንደ መርካቶ እና መገናኛ ባሉ ወንጀልና የህዝብ እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው አካባቢዎች በስፋት እንደሚተገበር ኮማንደር ደምስ ለታዲያስ አዲስ አብራርተዋል:: ይህ ቴክኖሎጂ የከተማዋን ደህንነት ለማስጠበቅ ትልቅ እመርታ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን÷ ህዝቡ ይህንን ዘመናዊ አሰራር ተጠቅሞ መረጃ በመስጠት የጸጥታ አካሉን ማገዝ እንዳለበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::














## አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እያደረገ ያለዉ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እያደረገ ያለዉ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ የተቋሙ አመራሮች እና ሰራተኞች ተናግረዋል::

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የ2018 ዓ.ም የስድስት ወራት የስራ አፈጻጸም ግምገማዉን የተቋሙ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋና ሌሎች አመራሮች እና ሰራተኞች በተገኙበት አካሄዷል::

ተሳታፊዎቹ በቀረበዉ የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ኤኤምኤን በቴሌቭዥን፤ በሬድዮ፤ በዲጂታል ሚዲያ፤ በጋዜጣ፤ በቴክኖሎጂ እና በሰዉ ሃብት ልማት ዘርፎች አመርቂ ዉጤት ማስመዝገቡን አንስተዋል::

ተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀረፉ የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ መሆኑን ተሳታፊዎቹ ገልጸዋል::አገልጋዩ፤ ዋርካና ጠረጴዛን የመሳሰሉ ፕሮግራሞች ህዝብ በቀጥታ የሚናገርባቸዉና የመልካም አስተዳድር ችግሮች የሚቀረፉበት መድረኮች በመሆናቸዉ የተጀመረዉ ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል::

ኤኤምኤን ምቹ የስራ አካባቢን ለመፍጠር፤ የሰዉ ሃይልን ለማብቃት፤ ዲጂታል አገልግሎትን ለማስፋፋት፤ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል እያደረገ ያለዉ ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ የተቋሙ አመራሮች እና ሰራተኞች ተናግረዋል::






## “ፉክክሩ ማን ከማን የበለጠ ሰረቀ?›› የሚል ሆነ::

ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት በሀገራችን ከኢኮኖሚ ዕድገት ባላነሰ ያደገዉ ሌብነት ነዉ:: ቡድናዊ የኢኮኖሚ የበላይነት ለፖለቲካ ኃይል የበላይነት እንደ ዋስትና ይቆጠራል:: በዚህ የተነሣ ሌብነት በደረቱ ከመሳብ ወጥቶ በራሪ ዘንዶ ሆኗል:: ዕድገቱ ደረጃ በደረጃ ወደ ሥርዓትነት ተቀየረ:: ተቋማትም ዋና ሥራቸዉን ዘነጉ:: ፉክክሩ ማን ከማን የበለጠ ሰረቀ? ከማን ጋር ብንሆን የበለጠ እንሰርቃለን? የሚል ሆነ:: መንግሥታዊ መዋቅሮች የሌቦች መደበቂያና የቀማኞች ዋሻ ሆኑ:: የልማታዊ መንግሥት መርሕ ተገርስሶ የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ሥርዓት በአንድ አግዳሚ ወንበር ተቀመጡ:: የፋይናን ተቋማት ተሟጠጡ:: የተፈጥሮ ሃብቶች በብላሽ ተዛቁ:: የጸጥታና የደኅንነት ተቋማት ወደ ኮንትሮባዲስትነት ተቀየሩ::

-



ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ


ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission


**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች


ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


**NCRS**

## ርዕሰ -አንቀፅ

# ሥነምግባር ግንባታ ሙስናን ለመከላከል ያለው ፋይዳ የላቀ ነው!

ሥነ-ምግባር ግንባታ (የሥነምግባር ትምህርትና አቅም ግንባታ) ሙስናን ለመከላከል ያለው ፋይዳ በጣም ትልቅ ነው:: ሙስና ብዙውን ጊዜ ከውጭ ህግና ቅጣት ብቻ ሳይሆን ከውስጣዊ የሞራል ድክመት፣ ከተሳሳተ እሴት ስርዓት እና ከግንዛቤ እጥረት የሚመነጭ ችግር ስለሆነ፣ ሥነምግባር ግንባታ ዋናውን ምክንያት የሚፈታ መፍትሄ ነው::

ዋና ዋና ፋይዳዎች (ጥቅሞች):- ውስጣዊ መርህ የሚፈጥር ነው ሰው ሙስናን ለመፈጸም የሚያደርገውን ውሳኔ "ይህ ተገቢ አይደለም" ብሎ ከራሱ ውስጥ እንዲቃወም ያደርጋል:: ህግ ብቻ ሲኖር ሰው "ካልተያዝኩ እኔ አይጎዳኝም" ይላል፤ ግን ጥሩ ስነ-ምግባር ግንባታ ካለው ደግሞ ይህን ብፈጽም ራሴን እና ህዝቤን እጎዳለሁ ብሎ ይቆጣጠራል:: የረጅም ጊዜ ባህል ለውጥ ያመጣል በትምህርት ቤት፣ በስራ ቦታ፣ በማህበረሰብ ውስጥ የሚሰጥ ስነ-ምግባር ትምህርት ትውልድን በቅንነት፣ በታማኝነት፣ በውጤታማነት እና በሀላፊነት ስሜት ያሳድጋል:: ይህም ሙስናን መደበኛ የሚያደርግ ባህልን ቀስ በቀስ ይሰብራል::

የግንዛቤና የአመለካከት ለውጥ ያመጣል፤ ሙስና ምንድን ነው? ለምን አደገኛ ነው? ለግለሰብና ለሀገር ምን ጉዳት ያደርሳል? የሚሉትን ጥያቄዎች በግልጽ ያስተምራል:: ይህም ሰዎች ሙስናን እንዲጠሉት፣ እንዲቃወሙትና እንዳይሳተፉበት ያደርጋል:: ህግን ከውስጥ የሚደግፍ ኃይል ይፈጥራል ህግ፣ ቁጥጥር፣ ቅጣት፣ ሽልማት ወዘተ ብቻውን ቢኖር ብዙ ጊዜ ውጤቱ ውስን ነው:: ስነ-ምግባር ግንባታ ግን ህጉን ከውስጥ የሚደግፍ የህሊና ግፊት ይፈጥራል:: ይህም ሙስናን መከላከልን የበለጠ ዘላቂ ያደርገዋል::

በተቋማት ውስጥ የመልካም አስተዳደር ባህል ይፈጥራል በፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ቦታዎች የሚሰጡ የስነ-ምግባር ስልጠናዎች መልካም አስተዳደርን ያጠናክራሉ፣ ብልሹ አሰራርን ይቀንሳሉ፣ እና ሰራተኞች ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ያደርጋል:: የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን (ፌ.ሥ.ፀ.ሙ.ኮ) በተደጋጋሚ የሚገልጸው ነገር፡ የሙስና መከላከል ስራ ከስነ-ምግባር ግንባታ ይጀምራል የሚል ነው:: ትውልድን በሥነ-ምግባር መገንባት፣ ተቋማትን በአሰራር ማጠንከር የሚለው መርህ በዚህ ላይ የተመሰረተ ነው::

በአጠቃላይ ስነ-ምግባር ግንባታ ሙስናን የሚከላከለው ከውጭ (ህግና ቅጣት) ብቻ ሳይሆን ከውስጥ (ህሊና፣ እሴት፣ ቅንነት) ጀምሮ ስለሆነ በጣም ወሳኝ እና ዘላቂ መፍትሄ ነው:: ሙስናን በተሟላ መልኩ ለመግታት ህግ፣ ቁጥጥር፣ ስነ-ምግባር ግንባታ አብረው መሄድ አለባቸው የሚል መልዕክት ኮሚሽኑ ያስተላልፋል::

## ኮሚሽኑ በመጀመሪያ ስድስት ወራት ያከናወናቸው ውጤታማ ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተገለጸ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በየደረጃው ከሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋር ገምግሟል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ ኮሚሽኑ በግማሽ ዓመቱ ለመከታተያ ክፍሎች በርካታ የአቅም ግንባታ ሥራ መሥራቱን ገልፀው፥ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል የተከናወኑ ውጤታማ ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል። በኮሚሽኑ የእቅድና በጀት ባለሙያ አቶ ግዛቸው ደገፉ የሥራ አፈፃፀሙን ባቀረቡበት ወቅት ኮሚሽኑ በግማሽ ዓመቱ ባከናወናቸው የትውልድ ሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ለ104 ሺህ በላይ አካላት ስልጠና መስጠቱን ገልፀዋል።

በ22ኛው ዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን የንቅናቄ መድረክን ጨምሮ በተለያዩ መድረኮች 1.5 ሚሊዮን ለሚደርሱ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ መፍጠር መቻሉን አስረድተዋል። ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ተናግረዋል። አቶ ግዛቸው አክለውም በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሙስና ጥቆማ አቀባበል ስርዓት በመዘርጋቱ ከ7,700 ካ.ሜ በላይ መሬትና ከ6 መቶ 77 ሚልየን ብር በላይ ገንዘብ ከምዝበራ ማዳን መቻሉንና በብልሹ አሰራር ውስጥ የተገኙ 718 አካላት ላይ እርምጃ መወሰዱን ገልፀዋል። የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ክፍሎች ቡድን መሪ ወ/ሪት ሐዋ አህመድ የመጀመርያ ሩብ ዓመት የድጋፍና ክትትል እና 22ኛው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን አከባበር ሪፖርት ቀርቦ ውይይት መካሄዱን ተገለልጽዋል።





## በአዲስ አበባ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ 52 ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወሰደ

የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ በህገ-ወጥ ተግባር እና በብልሹ አሰራር ላይ ተሰማርተው ባገኛቸው ሃምሳ ሁለት ሰራተኞች ላይ ጥብቅ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መውሰዱን አስታወቀ። ኤጀንሲው ይህንን እርምጃ ይፋ ያደረገው፤የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባን በሁሉም የከተማዋ ወረዳዎች ማዳረሱን በገለጸበት የስድስት ወራት የሪፖርት ግምገማው ላይ ነው።

ኤጀንሲው የአገልግሎት አሰጣጥ ግልጽነትን ለማረጋገጥ ባደረገው ጥብቅ ክትትል፤ በከባድ እና በቀላል የዲሲፕሊን ጉድለት ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ሰራተኞችን ለይቷል። በዚሁ መሠረት፤በድምሩ በሃምሳ ሁለት ሰራተኞች ላይ የቅጣት እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፤ከእነዚህም መካከል አስራ አምስቱ በፈጸሙት ከባድ ጥፋት ጉዳያቸው በህግ ተይዞ በፍርድ ቤት እየታየ ይገኛል። በተጨማሪም ሁለት ሰራተኞች ከስራ ሙሉ በሙሉ እንዲሰናበቱ ተደርጓል።

## የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 651 አመራርና ሠራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል - አገልግሎቱ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተጠያቂነትን ስርዓት ለማስፈን ባከናወነው ሥራ 651 አመራርና ሠራተኞች ላይ እርምጃ መውሰዱን ገልጿል። እርምጃ ከተወሰደባቸው አመራርና ሠራተኞች መካከል 13 የስንብት፣ 481 የደሞዝ ቅጣት፣ 157 የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መሆኑም ተጠቁሟል። በሌላ በኩል ተቋሙ ተግባራዊ ባደረገው የሙስና ጥቆማ ማቅረቢያ እና በሌሎች አማራጮች ከቀረቡት 311 ጥቆማዎች ውስጥ 270ዎቹ የማጣራት ሥራ መሰራቱን ገልጿል።

በቀረቡት ጥቆማዎች መሰረት በብልሹ አሰራር ጥፋተኛ መሆናቸው ከተለዩ አጠቃላይ 118 አመራርና ሠራተኞች መካከል በሂደት ላይ ያሉትን ጨምሮ በ75 ሠራተኞች ላይ ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተወስዷል። በዚህም 14 የፅሁፍ፣ 47 የደሞዝ ቅጣት፣ 2 ከቦታ ማንሳት፣ 5 ስንብት እንዲሁም 7 ጉዳያቸው ተጣርቶ ነፃ የተባሉ ናቸው።





## ባለፉት ስድስት ወራት ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ በተከናወኑ ተግባራት አበረታች ውጤት ተመዝግቧል - ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ

ባለፉት ስድስት ወራት ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ በተከናወኑ ተግባራት አበረታች ውጤት መመዝገቡን የሀረሪ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ ገልጸዋል። የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ ለሀረሪ ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ እንዳስታወቁት በክልሉ በመንግሥትና በሕዝብ ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል ሕዝብን ያሳተፈ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል። በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ በተከናወኑ ተግባራት ተጨባጭ ውጤት ማምጣት መቻሉን ገልጸዋል።



ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ የህብረተሰቡ ግንዛቤና ትብብር እያደገ መምጣቱንም አመላክተዋል። በዚህም ሃያ ጥቆማዎች አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ እና ሶስት ጥቆማዎች ደግሞ ጉዳያቸው በህግ አግባብ እንዲታይ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል። ለአብነትም ከ80 ሺህ ብር በላይ በጥሬ ብርና አምስት የቀበሌ ቤት የሕዝብና የመንግስት ሀብት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል ብለዋል።

በሌላ በኩል 1 ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑ ነባርና አዲስ የመንግስት ሠራተኞችን ሀብት በአዲስ መልክ የማስመዝገብ ሥራ መከናወኑንም አመላክተዋል። በተለይ በመንግስት ተቋማት እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ በማድረግና ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ሙስናን የመከላከል ተግባራት በስፋት ሲከናወን መቆየቱንም ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ ተናግረዋል። በቀጣይ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀው፤ ለስራው ስኬታማነትም የማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስገንዝበዋል።

## ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከር እንደሚገባ ተመላከተ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የክልሉን የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን አፈጻጸም ገምግሟል። የክልሉ ምክር ቤት የህግና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ፣ ብልሹ አስራሮችን ለመከላከል ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከር ይገባል ብሏል። የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወ/ሮ መሰረት ወ/ሰንበት እንዳሉት ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እየተሰራ ያለውን ተግባር በማጠናከር የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መረባረብ ያስፈልጋል።

ሀብት የማሳወቅና የማስመዝገብ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለው፥ ለሪፎርም ስራዎች ውጤታማነት የቅንጅት ስራዎችን ማጠናከር እንደሚገባ ተናግረዋል። የውስጥ ኦዲት አሰራርን በተመለከተ ወጪዎች በመንግስት ወጪ ደንብ መሰረት እንዲወጡ በማድረግ የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር ይገባል። በአገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከመቅረፍ ረገድ ቅንጅታዊ አሰራሮችን የበለጠ ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸዋል። የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንዳይባክን ለህዝቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በማጠናከር በሀብትና ንብረት የሚደርሰውን ምዝበራ ለመከላከል የህግ ማዕቀፍ አሰራሩን ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል።

ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለሀገር ዕድገት ነቀርሳ በመሆኑ የተጀመረው የልማትና የብልጽግና ጉዞ እንዳይቀለበስ በመረባረብ ለህዝቡ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በቁርጠኝነት መስራት እንደሚገባም መግለፃቸውን ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ማሞ ቴጋ እንደተናገሩት ሙስና የአንድን ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትን ወደ ኋላ የሚያስቀር በመሆኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሁሉም ሰው የበኩልን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል። በየተቋማቱ የዘርፉን የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች በቋሚነት በመመደብ እና በኃላፊነት እንዲሰሩ ከማድረግ አንፃር ያለውን ክፍተት ለመቅረፍ እየተሰራ ነው። የፀረ-ሙስና ትግልን ውጤታማ ለማድረግ በቅንጅት እየተሰራ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፥ በቀጣይ የህግ አሰራሮችን በማጠናከር ወንጀልን ለመቀነስ በቁርጠኝነት ይሰራል ብለዋል።



# ሳይቃጠል በቅጠል

## ፖለቲካዊ ሙስናን የመከላከያ ዘዴዎች

ሙስና ከሰው ልጅ ማህበረሰብ ከተፈጠረ ጀምሮ የኖረ እና በዘመናት የተስፋፋ ችግር ነው። በተለይ ፖለቲካዊ ሙስና (Political Corruption) ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሮችና የመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚፈጸም የሙስና ዓይነት ሲሆን፣ ስልጣንን ለግል ጥቅም፣ ለፓርቲ ጥቅም ወይም ለቡድን ጥቅም በመጠቀም የህዝብን ጥቅም የሚያፈነግጥ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችን የሚያዛባና የዴሞክራሲ ሂደትን የሚያዳክም ነው።

ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ቅርጾችን ይዞ ይታያል። እንደ የፖለቲካ ፋይናንስ ግልፅነት እጥረት፣ የጥቅም ግጭት(conflict of interest)፣ የሀብት ይፋ ማድረግ አለመሟላት፣ የተቋማት ገለልተኝነት እጥረት፣ የፖለቲካ ሹመት በቅርበት/በገንዘብ መሰረት መሆን ወዘተ። ይህ ሁሉ የህዝብ እምነትን ያጣል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያዘገያል፣ የፍትሕና የእኩልነት ስሜትን ያበላሻል፣ በመጨረሻም የሀገር ሰላምና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ስጋት ይፈጥራል።

ይህን ችግር ሳይስፋፋ መከላከል የሚቻለው በግልፅነት፣ በተቋማዊ ገለልተኝነት፣ በጠንካራ ህግ አስከባሪነት፣ በህዝብ ተሳትፎና በፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ብቻ ነው። ፖለቲካዊ ሙስና (political corruption) ሳይስፋፋ ለመከላከል የሚቻሉባቸው ዋና መንገዶች በተለምዶ በተለያዩ ሀገራት ልምድና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንደ (Transparency International፣ World Bank፣ UNODC፣ OGP) በተሰጡ ምክረሀሳቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህን መንገዶች በተግባር ላይ ማዋል በተለይ ፖለቲካዊ ፈቃደኝነትና ተቋማዊ ጥንካሬ ይፈልጋል።ፖለቲካዊ ሙስናን ለመከላከል ውጤታማ የሆኑ ዋና መንገዶች፦

ግልፅነት (Transparency) ማረጋገጥ: የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጭና ወጪ (political finance) ሙሉ በሙሉ ይፋ መሆን፣ የመንግስት ውልና ግዥ (public procurement) ሂደት ክፍት እና በመስመር ላይ መታየት (open contracting) እና የበጀት ወጪና የፕሮጀክት ሂደት ለህዝብ መገለጥ ናቸው።

ግጭት የሚያስከትሉ ጥቅሞችን መከላከል (Conflict of Interest rules):- ባለስልጣናት ግላዊ ንብረት ከስራቸው ጋር ግንኙነት እንዳይኖር መገደብ፣ የቤተሰብ ንግድ ከመንግስት ጋር ንግድ እንዳይደረግ መከልከል።የሀብት መግለጫ እና ማረጋገጫ ስርዓት (Asset declaration & verification) :ባለስልጣናት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት፣ በሥራ ውስጥ እና ከዚያ በኋላ ሀብታቸውን መግለፅ፣ ይህን ማረጋገጥ የሚችል ገለልተኛ ተቋም መኖር አለበት።

ጠንካራ እና ገለልተኛ የፀረ-ሙስና ተቋማት መገንባት: የፌዴራል ወይም ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን፣ የፍርድ ቤት፣ ፖሊስና ማጣራት ተቋማት በተመሳሳይ ገለልተኛነት።የፖለቲካ ፋይናንስ ጥብቅ መቆጣጠሪያ: የበጎ ፈቃደኛ የገንዘብ አስተዋፅዖ መጠን መገደብና ከመንግስት ጋር ውል ከሚያደርጉ ኩባንያዎች የፖለቲካ ልገሳ መከልከል።

የመረጃ ነፃነት እና የፕሬስ ነፃነት ማረጋገጥ: ጋዜጠኞችና የሲቪል ማህበረሰብ ሙስናን ሲያጋልጡ ጥበቃ ማድረግ፣ የመረጃ መጠየቂያ ህግ (Freedom of Information Act) ተግባራዊ ማድረግ። የህዝብ ተሳትፎ እና የውስጥ ማሳወቂያ (Whistleblower protection) : ሙስናን የሚያጋልጡ ሰዎችን ከተቃራኒ ጥቃት መጠበቅ፣የውስጥ ማሳወቂያ ስርዓት መፍጠር።ዲጂታል ቴክኖሎጂ መጠቀም፤ ኤሌክትሮኒክ ግዥ፣ዲጂታልክፍያ፣blockchain በመጠቀምዱካመከታተል፣የገንዘብ ዝውውርክካሽ ወደ ባንክ ማዛወር።የሥነ ምግባር ትምህርትና ባህል መገንባት: በትምህርት ቤት፣ በሲቪል ሰርቪስ እና በፖለቲካ ውስጥ የሙስና አሉታዊነት ማስተማር፣ከፍተኛ ባለስልጣናት “Tone at the top” በማሳየት ምሳሌ መሆን።ጠንካራ ቅጣትና ፈጣን ፍርድ: ሙስና የተፈጸመ ሰው ቅጣቱ በቂ እና ፈጣን መሆን፣የተያዙ ሀብቶች መቀየር (asset recovery) ናቸው:
: በአጠቃላይ፣ ፖለቲካዊ ሙስናን መከላከል በአንድ ነገር ብቻ አይቻልም፤ ግልፅነት፣ ጠንካራ ተቋማት፣ ህዝባዊ ተሳትፎና ፖለቲካዊ ፈቃደኝነት አንድ ላይ ሲሰሩ ብቻ ዘላቂ ውጤት ያስገኛል።

ቆይታ

# ለመንግስት ከፍተኛ አመራሮች ሥልጠና ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራ ተሰርቷል - አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ



የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2018 በጀት ዓመት ለማከናወን በእቅድ ከያዛቸው ዓበይት ተግባራት መካከል መንግስት ሙስናን ለመዋጋት በሰጠው ትኩረት መሰረት ለከፍተኛ አመራሮች ሥልጠና በመሥጠት የፀረ-ሙስና ትግሉን በባለቤትነት እንዲመሩት ማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም 27 ዘርፎችን ለሚመሩ 1200 ለሚሆኑ የፌደራል ከፍተኛ አመራሮች ሥነ-ብግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር በሚል ርዕስ ከየካቲት ወር ጀምሮ ሥልጠና ለመሥጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቋዋል፡፡

በዚህ ዙሪያ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ከኮሚሽኑ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥልጠና መሪ ሥራ አስፈጻሚ ጋር አጭር ቆይታ አድርጋለች፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በመጀመሪያ መረጃ ለመስጠት መካከላችን ስለተገኙ እያመሰገንኩ እስኪ ራስዎን ያስተዋውቁ፣

የእለቱ እንግዳ ስሜ አቶ የኂላእሸት ይባላል በፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥልጠና ተጠባባቂ መሪ ስራ አስፈጻሚ ነኝ፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የሥልጠናው ዋነ አላማ ምንድ ነው?

አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ፡- በመንግስት ተቋማት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ለዜጎች አገልግሎቶችን በሚሰጡበት ወቅት ከኃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊያስገባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን ለመከላከል እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንኑ በስልጠና ማዳበር በማስፈለጉ "ስነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት መከላከል እና ማስተዳደር" በሚል ርእስ ስልጠና ተዘጋጅቷል፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ሥልጠናውን ለከፍተኛ አመራሮች መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድነው?

አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ፡- የጥቅም ግጭት በዋናነት ከውሳኔ ሰጪነት ጋር ይያያዛል፤ ከፍተኛ አመራሮች ደግሞ ከተሰጣቸው ሃላፊነት አንጻር ሰፊ የመወሰን ፈቃደ ስልጣን (Discration Power) አላቸው፡፡ አመራሮች ዛሬ የሚወስኑት ውሳኔ ነገ ወደ ተግባር ተቀይሮ በሀገር ላይ፣በተቋማትና በዜጎች ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳርፋል፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ አመራሮች በውሳኔያቸው ሂደት በጥቅም ግጭት አማካኝነት ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር በመከላከል ግንባር ቀደም ሆነው በተቋማቸው ስነምግባር ባህል ሆኖ እንዲገነባ ለማድርግ ከሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭትን በመከላከል ዙሪያ ለአመራሩ የእውቀት፣የክህሎት እና የአመለካከት ግንባታ ስልጠና መስጠት ወቅታዊ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ከሌሎች የሥልጠና ርዕሶች ይልቅ የጥቅም ግጭት ለምን ተመረጠ?

አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ፡- የጥቅም ግጭት በራሱ ሙስና ባይሆንም በአግባቡ ካልተመራ በስተቀር የመወሰን ሀላፊነትን በመፈታተን ሙስና እንዲከሰት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ይህን የማስተዳደር ሃላፊነት ከሁሉም ባላይ በአመራሩ ጫንቃ ላይ የወደቀ በመሆኑ ይህን የሥልጠና ርዕስ ለመምረጥ አሳማኝ ምክንት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የሥልጠናውን ቅድመ ዝግጅት ባጭሩ ቢያብራሩልን?

አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ፡- በቅድመ ዝግጅት ሥራው የሞጁል ዝግጅት፣ የአሰልጣኝ ምልመላ፣ የስልጠና ተሳታፊዎች ልየታና የማሳወቅ ስራን ያካትታል፡፡ የሥልጠና ሞጁሉ በሀገር በአቀፍ ፀረ-ሙስና ምርምር ትስስር ምሁራን ተዘጋጅቶ ጥራትን ተገቢነቱን ለማረጋገጥ ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተገቢነት ግምገማ (validation)

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- አልጣናውን የሚሰጡት አካላት እነማን ናቸው? እንዴትስ ተመረጡ?

አቶ የኂላእሸት ኮሚሽኑ ምሁራንን በጸረሙስና ትግል ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ሀገራዊ ሀላፊነታቸውን የሚወጡበት እድል አመቻችቷል፤ ከዚህ አኳያ ከልዩ ልዩ ከፍተኛ ትምህርት የተወጣጡ ምሁራን በጸረሙስና ምርምር ትስስር ውስጥ አባል ሆነው በሥነምግባር ግንባታ እና ሙስናን በመከላከል በጥናትና ምርምርና በስልጠና ከኮሚሽኑ ጋር እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ለከፍተኛ አመራሩ የሚሰጠውን ስልጠና ሞጁል ያዘጋጁትም እነዚህ ምሁራን ሲሆኑ ስልጠናውንም የሚሰጡት እነሱ ናቸው፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ስልጠናው መቸ እና በምን መልኩ ሊሰጥ ታስቧል?

አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ፡- ሥልጠናውን ከየካቲት እስከ መጋቢት 2018 ዓም ተሰጥቶ የሚጠናቀቅ ሲሆን ስልጠናው በየዘርፉ ኮሚሽኑ በሚመድባቸው አሰልጣኞች የሚሰጥ ሲሆን ከስልጠና በኂላ የሚደረገ ውይይቶች በዘርፉ ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች እና በኮሚሽኑ የስራ ሃላፊዎች የሚመራ ይሆናል፡፡

የፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን!!



አቶ የኂላእሸት ደሳለኝ

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚደረገው ማንኛውም የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት እና በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ፣ የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን፣ የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ለሌላ ሰው ያስገኘ፣ በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ፣ ያቀረበ እንደሆነ፤ በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ፣ ከማንኛዉም የመንግስት እና ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላትን በማጠናቀር መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የሚደረግበት ነው፡፡

በመሆኑም ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ውጪ የባንክ ሥራ በመስራት ኢትዮጵያ ከ14 ሚሊየን ዶላር በላይ እንድታጣ በማድረግ የተጠረጠረችው ቻይናዊት ግለሰብ ክስ ተመሰረተባት፡፡ ሊንግ ቹንግ የተባለችው ተከሳሽ በተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚገኙ ሰዎች ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ሲፈልጉ በእነዚያ ሀገራት ከሚገኙ ያልተያዙ ግብረ አበሮቿ ጋር ገንዘቡን



በመሰብሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ 10 ግለሰቦች ሲያስተላልፉ መቆየታቸው በክሱ ላይ ተመላክቷል፡፡

ተከሳሿ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በከፈተችው የሂሳብ ቁጥር በመጠቀም ከሕዳር 30/2013 ዓ.ም እስከ ሕዳር 4/2018 ዓ.ም 1ሺህ 112 ጊዜ በአጠቃላይ ብር 636 ሚሊየን 157 ሺህ ብር ለተለያዩ ግለሰቦች ማስተላለፋቸውን ዐቃቤ ሕግ በክሱ አስረድቷል፡፡ ይህ ህገወጥ የባንክ ስራ ገንዘቡ በህጋዊ የገንዘብ አስተላላፊዎች በኩል ቢተላለፍ ኢትዮጵያ ታገኝ የነበረውን 10 ሚሊየን 492 ሺህ ዶላር አሳጥቷታል ብሏል፡፡

በተጨማሪም በአቢሲኒያ ባንክ በስሟ በከፈተችው የሂሳብ ቁጥር በመጠቀም ከሕዳር 10/ 2014 ዓ.ም እስከ ሕዳር 04/2018 ዓ.ም ድረስ ከ201 ጊዜያት በላይ በድምሩ 233 ሚሊየን 433 ሺህ ብር ለተለያዩ ግለሰቦች ማስተላለፏን ክሱ አመላክቷል፡፡ ይህ ገንዘብ በባንኮች ወይም በህጋዊ መንገድ ቢላክ ኖሮ ሀገሪቱ ታገኝ የነበረውን 4 ሚሊየን 37 ሺህ ዶላር ማሳጣቷንም ዐቃቤ ሕግ አስረድቷል፡፡ ግለሰቧ ከውጭ ሀገራት ገንዘብ ለተላከላቸው ሰዎች በአጠቃላይ ከ839 ነጥብ 59 ሚሊየን ብር በላይ በህገወጥ መንገድ በማስተላለፍ ኢትዮጵያ ልታገኝ የነበረውን ከ14 ነጥብ 5 ሚሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ በማድረግ ተጠርጥራ ክስ ተመስርቶባታል፡፡ የክስ መዝገቡን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ልዩ ልዩ ወንጀል ችሎት ሲሆን፥ ግለሰቧ ከብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ውጪ የባንክ ስራ በመስራት ወንጀል ክስ ተመስርቶባታል፡፡ በዚህም በ2017 ዓ.ም የወጣውን የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 አንቀጽ 2 (6) መ እንዲሁም አንቀጽ 90 (1) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የወንጀል ድርጊቱን ፈጽማለች ሲል ዐቃቤ ሕግ ለችሎቱ አስረድቷል፡፡

በሌላ የሙስና መረጃ የደቡብ ኮሪያው ፍርድ ቤት፣ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ባለቤት የሆኑትን ኪም ኬዮን ሂ በሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ብሎ በመፍረድ የ1 ዓመት ከ8 ወር እስራት ወስኖባቸዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የቀድሞዋን እመቤት ለእስር የዳረገው፣ ከ"ዩኒፊኬሽን ቸርች") ከተሰኘ የሃይማኖት ተቋም እና ከሌሎች አካላት ጋር በመመሳጠር ጉቦ ተቀብለዋል በሚል ነው፡፡ 200,000 ዶላር የሚገመት ገንዘብ እና የቅንጦት ስጦታዎችን (ሁለት የሻኔል ቦርሳዎች እና የዳይመንድ ሐብልን ጨምሮ) ተቀብለዋል ተብሏል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ፣ የአክሲዮን ዋጋ በማጭበርበር እና የፖለቲካ ፈንድ ሕግን በመጣስ ከቀረበባቸው ክስ ነጻ እንደሆኑ ወስኗል፡፡

ይህ የተሰማው ባለቤታቸው የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዮን ሱክ ዩል እ.ኤ.አ በ2024 በሀገሪቱ "ማርሻል ሎው" (ወታደራዊ አገዛዝ) በማወጅ ህገወጥ ተግባር ፈጽመዋል ተብለው ከስልጣን ተወግደው የ5 ዓመት እስራት ከተፈረደባቸው በኋላ ነው፡፡ የቀድሞው ፕሬዚዳንት በሌላ ክስ የሞት ቅጣት ሊጠብቃቸው እንደሚችልም የሲኤንኤ ዘገባ አመልክቷል፡፡ በተያያዘ ዜና የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሃን ዱክ-ሱ ለፕሬዚዳንቱ ህገወጥ ተግባር ተባባሪ ነበሩ በሚል ከቀናት በፊት የ23 ዓመት እስራት እንደተፈረደባቸው ይታወሳል፡፡

**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

## መልካም ዜና

### በታማኝነታቸው በአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ እውቅና ያገኙት-አቶ አማረ ታደሰ

አቶ አማረ ታደሰ ከ200 ሺህ ዶላር በላይ ለባለቤቶች በመመለስ በልዩ ታማኝነት የአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ እውቅናን አግኝተዋል፡፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ለ30 ዓመታት ያገለገሉት አቶ አማረ ታደሰ፣ ለሰው ልጅ የታማኝነት ትርጉም ምን እንደሆነ በተግባር ያስመሰከሩ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአጠቃላይ ከ442,000 የአሜሪካ ዶላር በላይ የሚገመት ገንዘብና ንብረት ወድቆ አግኝተው ለባለቤቶቹ በመመለስ ይታወቃሉ፡፡

ከእነዚህም መካከል በከለር ማዳበሪያ ተጠቅልሎ በላውንጅ ውስጥ የተረሳ 200,000 ዶላር፣ ቼኮችን ጨምሮ 236,000 ዶላር እና ሌሎችም ተጠቃሽ ሲሆኑ፣ አቶ አማረ ገንዘቡን ሲያገኙ የባለቤቶቹን ጭንቀት በመረዳት ያለምንም ማመንታት ለሚመለከተው አካል ያስረክቡ ነበር፡፡ይህ አስደናቂ ስብዕናቸው የመነጨው ከልጅነት አስተዳደጋቸው ሲሆን፣ ገና በ8 ዓመታቸው መንገድ ላይ ያገኙትን ገንዘብ ለባለቤቱ በመመለስ ታማኝነታቸውን መለማመድ ጀምረዋል፡፡ አቶ አማረ ላሳዩት ልዩ ታማኝነት ከአየር መንገዱ የዓመቱ ምርጥ ሰራተኛ ሽልማትን እንዲሁም የአፍሪካ ድንቅ ድንቆች መዝገብ (Book of Africa Records) እውቅናን አግኝተዋል፡፡

ይህን ሁሉ ሃብት የመለሱት እኚህ ታማኝ ሰው፣ ዛሬም ድረስ የራሳቸው የግል ቤት የሌላቸው ቢሆንም፣ ባደረጉት መልካም ተግባር የሚሰማቸው ደስታ ግን ከምንም በላይ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ አሁን ላይ "ፈተና ያልበገረው ታማኝነት" በሚል ርዕስ የህይወት ታሪካቸውን የያዘ መጽሐፍ ለማሳተም በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡




### በጎንደር ከተማ ወድቆ ያገኙትን አይፎን ስልክ ለባለቤቱ የመለሱት እናት

በጎንደር ከተማ በጽዳት ባለሙያነት ተቀጥረው የሚሰሩት ወ/ሮ አገኘሁሽ አሰፋ ዛሬ ጠዋት ከተራ እና ጥምቀት የሚከበርበትን ስፍራ በማጽዳት ተግባር ላይ ሳሉ አይናቸው መሬት ላይ የወደቀ እጅግ ዘመናዊ እና ውድ የሆነ አይፎን ስልክ ላይ ያርፋል፡፡

ስልኩን አንስተው ባለቤቱ እስኪደውል መጠባበቅ ይጀምራሉ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስልኩ ጠራ፤ ፈጥነው ስልኩን ሲያነሱትም "ሰላም እንዴት ነዎት እመቤት ያገኙት ስልክ እኔ የማስጎበኛቸው እንግዳ ስልክ ነው" የሚል መልዕክት ይሰማሉ፡፡ ወይዘሮዋም በተረጋጋ መንፈስ "ባለቤቱ ደውሎ ስልኩን ለመመለስ ተዘጋጅቼ እየተጠባበቅሁ ነው" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ይህንን ምላሽ የሰሙት የስልኩ ባለቤት ብዙ ነገራቸው ከስልካቸው ጋር በመያያዙ መደናገጥ ውስጥ ገብተው የነበሩት የውጭ ሀገር ዜጋ ደስታቸው እጅግ ከፍተኛ ሆነ፡፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ስልኩ የጠፋባቸው እንግዳ ወ/ሮ አገኘሁሽ ወደሚሰሩበት ቦታ ደርሰው ስልካቸውን ተረከቡ፡፡

ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ወድቆ ያገኙትን ስልክ በታማኝነት ለባለቤቶቹ የመለሱት ወ/ሮ አገኘሁሽ አሰፋ፤ በአሁኑ ገጠመኝ ጥምቀትን በጎንደር ሊባረክ የመጣ የውጭ ሀገር ሰው ሊከፋው አይገባም በሚል በፍፁም መታመን ለባለቤቱ በመመለሴ ደስተኛ ነኝ ብለዋል፡፡ ያልደከሙበትን የራስ ለማድረግ ማሰብ ተቀባይነት የሌለው ተግባር መሆኑን በመግለጽ፤ ከምንም በላይ ለራስ መታመን በፈጣሪ ዘንድ የተወደደ ተግባር ነው በማለት ተናግረዋል፡፡

ጥምቀትን በጎንደር ለማክበር ከመሰሎቹ ጋር የመጣው አሜሪካዊው ጃፍ በጉብኝት ወቅት ምስል ለማስቀረት ስልኩን ሲፈልግ ነበር ስልኩ እንደወደቀበት ያወቀው፡፡ነገር ግን ወደ ስልኩ በሚደውሉበት ወቅት ወ/ሮ አገኘሁሽ አሰፋ ቀና ምላሽ በመስጠት ስልካቸውን የመለሱላቸው በመሆኑ እጅግ በመደሰት ከፍተኛ ምስጋና ማቅረቡን ለፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን ገልጸዋል፡፡ በፍጹም ታማኝነት የተመለሰለት ስልክ በርካታ መረጃ መያዙን በመጥቀስ፤ ጥምቀት የማይረሳ ገጠመኝ እንደተወላቸው ተናግረዋል፡፡



# ኪነ-ጥበብ

## ጭውውት

ባንድ ወቅት አንድ ተገልጋይ ጉዳይ ለማስፈፀም ከአንድ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ዘንድ ይሄዳል፣ ነገር ግን መ/ቤቱ እንደደረሰ ከአንድ ሰው በቀር ማንንም አላገኝም።

ባለጉላይ፡- ከኃላፊው ጋር ቀጠሮ ነበረኝ አልገቡም?

ሰውዬው፡- ስብሰባ ላይ ናቸው ይለዋል።

ባሉዳይ፡- ምክትሉ የሉም?

ሰውየው፡- እሳቸውም ፊልድ ወጥተዋል።

ባሉዳይ፡- ፀሐፊዋስ የለችም?

ሰውየው፡- እርሷም ለሻይ ረፍት ወጥታለች?

ባለጉዳይ፡- መቼ ይመለሳሉ?

ሰውየው፡- ይቆያሉ፣ ለመሆኑ ችግረዎት ምንድን ነው? እንድረዳወት፣

ባለጉዳይ፡- ችግሬማ ፍርድ ተጓደለ ድሀ ተበደለ፣ የስራ አጥ ቁጥር ጨመረ

ትውልድ ባከነ መፍትሄው ምንድን ነው ለማለት ነው።

ሰውዬው፡- እሱ አያሳስበዎት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል አንድ ምርጥ አቅድ አቅደናል በዚህ ካልተፈታ ሁለተኛ ወደር የለሽ እቅድ አቅደናል፣ እሱም ካልፈታው ሌላ ሦሥተኛ እቅድ አዘጋጅተናል፣

ስለዚህ እጅ በእጅ ተጋግዘን እናሳካዋለን በማለት ይመልሳል።

ባለጉዳይ፡- ለመሆኑ የእርሰዎ የስራ ድርሻ ምንድ ነው ብለው ይጠይቁታል

ሰውዬው፡- እኔም ባለጉዳይ ነኝ፣

ባለጉዳይ፡- ታዲያ እንዴት በሌለ ሥልጣን ሰውን ያማልላሉ?

ሰውየው፡- ኃላፊዎች እስኪመለሱ የገፅታ ግንባታ ስራ ልስራ ብየ ነው፣ አለ ይባላል።